መስከረም 19 ቀን 2001 ዓ.ም/

# ከ1983 ዓ.ም ጀምሮ ኢትዮጵያን እየገዛ ያለው ማን ነው?

# "ኢሕአዴግ" ማን ነው? እነሆ፣ ጥያቄዎቼ ለገብሩ አሥራት

(ከአያልነሽ -ክፍል 2)

የተከበራችሁ አንባቢዎች ሆይ!

ባለፈው የክፍል አንድ ጽሁፌ ላይ አንጠልጥዬ የተውኳቸው ጥያቄዎች ነበሩኝ፤ እመለስባቸዋለሁ ብዬ ቃል ገብቼ መለየቴንም አስታውሳለሁ። ቃል አባይ (ባ) ላላ ብላ ትነበብልኝ እንዳልባል - እነሆ! ከጥያቄዎቼ ጋር ተመልሼ መጥቻለሁና አባካችሁ፣ ጥያቄዎቼን አብራችሁ እንድትጠይቁና የጥያቄዎቼን ዚቅ ትመረምሩልኝ ዘንድ አንባቢዎቼን ከአክብሮት ጋር በትህትና እጠይቃለሁ።

"ኢሕአዴግ" የተባለው ተቋም ምንድን ነው? ወያኔዎች ዛሬ የሚያሞናሙኑት "ኢሕአዴግ" ንብረትነቱ እውነት የኢትዮጵያ ነው ወይስ የወያኔ? የዚህ ድሪቶ ደራችና መሐንዲስ ማን ነው? በዚህ በኢትዮጵያ ስምስ የተጀቦኑት "ኢሕአዴጋውያን" እነማን ናቸው? እነኝህ "ኢሕአዴጋውያን" (ከትግራይ ውጭ) በኢትዮጵያ ከተበተኑ ጀምሮ ሀገረ-ኢትዮጵያን የጠየቋት ምንድን ነው? የሚሉትንና የመሳሰሉትን ጥያቄዎች የወያኔን መሥራችና የ"ኢሕአዴግን" ወላጅ ገብሩ አሥራትንና ሸሪኮቻቸውን አሁንም መጠየቄን አላቆምኩም።

ህወሓት/ወያኔ፣ ደርብ፣ ደርብ፣ እያሉ ዛሬ እነገብሩ ከበሮ የሚደልቁለት ይህ "ኢሕአዴግ" የሚባለው ማን ነው? እስቲ ከ 17 ዓመት በኋላ እነኝህን "ኢሕአዴጋውያንን" - የወያኔ ስጦታዎች - ተመልሰን እንቃኛቸው። "<u>በጥባጭ ካለ ማን ጥሩ ይጠጣል</u>" ተብሎ የለ! ከቀሰቀሱን ይኸው ነቅተናልና ታሪክን አጣቅሰን አንድ ልንላችሁ መጥተናል እንላችዋለን።

<u>ሕወሓት (ሕዝባዊ ወያኔ ሓርነት ትግራይ) ወያኔ፥</u> ይህ ድርጅት የእነገብሩ አሥራት/ስዬ አብርሃ እናት ድርጅት ሲሆን፣ የተቋቋመው በ1967 ዓ.ም ትግራይ ውስጥ ነው፤ ዘንድሮ 33 ዓመቱን አከበርኩ ብሎናል።

የዚህ ድርጅት ዓላማና መርሃ ግብር "ትግራይ ተጨቁኗል" ይልና እንደሰሙ ትግራይ "ሓርነት" ማግኘት አለባት ባይ ነው። ይህ እነስዬ በውስጣቸው የሚያስቡት እጅግ በደም ሥራቸው ዘልቆ የገባ፣ የወያኔዎች በአጠቃላይ የውስጥ ደዌ በሽታቸውና ፍልስፍናቸው ነው። ልብ በሉ አንባቢዎች! ወያኔ 33 ዓመት የሰው ሕይወት የገበረው ብታምኑም ባታምኑም እነስዬ በነገሩንና ሲነግሩን በቆዩት "በአማራ" የተያዘውን የትግራይን ሕዝብ "ሓርነት" ወይም ነጻነት

ለማቀዳጀት ነው አራት ነጥብ። ሕዝባዊ ወያኔ ሓርነት ትግራይ(ወያኔ) ኢትዮጵያ የምትባል ሀገር ቀደም ብላ ያልነበረች ነች፤ አሁን አለች የምትባለው ደግሞ 100 ዓመት ያልሞላት "አማራው" የሠራት እንቅብ ናት ይለናል። ታዲያ ይህንን የእነርሱን "ወርቅ" የሆነ ዘር ከአማራው "ሓርነት" ያወጡት ዘንድ ይህ ወያኔ የተባለውን "የትግራይ ነጻ" አውጭ ዝግንትል ወለዱ ማለት ነው። ሌላው አብዚሎ-ከምዚሎ የሚሉት ትርፍ ነው። አዎ! እነሰዬ ዛሬ አይናገሩት እንጂ ለወያኔ አባልነት የሚመለምሏቸውን/የመለመሏቸውን የትግራይ ልጆች ጭንቅላት ያጠቡትና ያስታጠቁት፣ ይሄንን - "በአማራ" ተጨቁነኃል የሚል የጠባብ ብሄርተኝነትን ነቀርሳ ነው። አዎ! በርካታ የትግራይ ልጆችም በዚህ በሽታ እንዲለከፉ አድረገዋል። ለእነኝህ የትግራይ ልጆች ግን አሁንም የምላቸው ለእኔም ሆነ ለአብርኸት፣ ለሌሎችም ወዘተ...፣ ኢትዮጵያዊነትን ሰጪና ነሽ ማንም ሊሆን አይችልም እላቸዋለሁ። ኢትዮጵያዊነትን ያገኘነው ሁላችንም በውልደት በተፈጥሮ ነው። ኢትዮጵያ የምትባል አገር ውስጥ ተወለድን። አለቀ። ለእኔ ይሄ ነው ቁምነገሩ። ይልቁንስ እኔም ሆንኩ እናንተ የትግራይ ልጆች፣ እነሰዬ ከየት መጣን እንደሚሉ በሹሉክሉክ ሳይሆን በድፍረት በአደባባይ እንዲነገሩን ወጥረን መያዝ አለብን እላችኋለሁ - ከአክብሮት ጋር። በወያኔ የተፈጸመውና የሚፈጸመው በደልና ግፍ ደግሞ ወደዳችሁም ጠላችሁ በትግራይ ህዝባችን ስም በወያኔ አማካኝነት የሚከናወን ተግባር ነውና፣ ኢትዮጵያችን ውስጥ አሁን መሬት ላይ ያለና የሚታይ ሐቅ ነው። እነሰዬና ገብሩ፣ ለገሰ ዜናዊ እስኪያባርራቸው ድረስ፣ ከ"ወርቁ ዘር" በመፈጠራችን እያሉ በኩራት ተንጠባርረው ህዝብን አንዱን "ወርቅ" ሌላውን "ጨርቅ" በማለት ይህንን ስር የሰደደ የጠባብነትና የዘረኝነት በሽታቸውንና ሕዝብን ከሕዝብ የሚያናክስ ዛራቸውን በአደባባይ የ"አማራ" መናገሻ ከተማ ነች ባሏት አዲስ አበባ ላይ ሲናገሩት የነበረ፣ የአንደበታቸው መፍቻ ቃል ነበር። በአንፃሩ የናዚው ሒትለር ይህንን ዘረኛና ፋሽስት የሆነ ብሔርተኛነት ድርጊቱን ሊፈጽም ሲነሳ ዋናና መሪ መፈክሩ ያደረገው "ጀርመን ለጀርመኖች" የሚል ነበር። ሒትለር በዚህ መሪ መፈክሩ የሄደበት መንገድ እንደሕዝብ ጀርመኖችን በሕይወት ብዙ አስከፍሎ፣ እሳከአሁንም በዓለም የታሪክ ማህደር ጥቁር ነጥብ አስመዝግቦባቸው አልፏል። የሁለቱም፣ የናዚው "ጀርመን ለጀርመኖች" የሚለው ብሄርተኛ የሆነው መፈክርና የወያኔው ሰዬ/ገብሩ የጠባብ ብሄርተኝነት/መንደርተኝነት መፈክሮች፣ በየትኛውም መመዘኛ ሁለቱም አደገኞችና የሰውን ልጅ የተፈጥሮ መብት የሚጨፈልቁ ናቸው። ሁለቱም ምርጫ ውስጥ የሚገቡ አይደሉም። በመሆኑም ጀርመኖች በያኔው ጦስ ሳቢያ፣ ዛሬ በኢኮኖሚ

*አድገውና በልጽገው፣ ትልቅ ተብለው ከሚጠሩት የምዕራብ አገሮች ተርታ ተሰልፈው እያለ፣ ያ የታሪክ ጠባሳ የውስጥ ቅሪት ሆኖ ከቁስላቸው ጨርሰው አላገገሙም። በነገራችን ላይ ዛሬ ጀርመን ውስጥ ሒትለር የሚል ስም እንዳይሰጥና እንዳይሰየም፣ በሕግ ተደንግጓል፣ - ልክ ነው? እባካችሁ! ጀርመን የምትኖሩ ኢትዮጵያኖች አንድ በሉኝ። አስታውሱ! የእኛዎቹ ጉዶች ግን እስካሁን ለሠሩትና ላደረጉት ሀገርን የማናጋትና በህዝብ ላይ ላደረሱት በደል ሳይሰቀጥጣቸውና ይቅርታ እንኳን ሳይጠይቁ፣ ሌላ ቡቱቶ ለብሰው ዓይናቸውን በጨው አጥበው የሚጠሏትን ኢትዮጵያ ጨርሰው ሊያፈርሱ ጫማ ሲጨርሱ ይታያሉ።*

*እነኝህ በጠባብነትና በጎጥ ዛር የተለከፉት ወያኔዎች፣ በ1983 ዓ.ም የኢትዮጵያ ዋና ከተማ ወደ ሆነችው አዲስ አበባ ሲገቡ፣ ሕወሓት/ወያኔ "የትግራይ ሓርነት" ብሎ ምንልክ ቤተ -መንግሥት መግባት አያስችላቸውም ነበርና፣ ግዴታ አንድ ድሪቶ ማሰፋት ወይም መደረት ነበረባቸው። እናም "ኢሕአዴግ" የሚል መጫሚያ በእነ ኮኽን ተባርኮ፣ ያንን ተጫምተው አዲስ አበባ ዘለቁ።* ***<u>ኢትዮጵያ</u>*** *የተባለውን ክቡር ቃል ያላወቁትና ያጣጣሉት ወያኔዎቹ እነ ሰዬ/ገብሩ እንጅ፣ ፈረንጆችማ ከቀደሞው ስህተታቸውና ታሪካቸው ተምረዋልና አሽከሮቻቸውን አስግረው አሣውን ለማጥመድ፣ ዘዴውን አፈላልገው አላጡትም ነበር። ለዚህም ነው አርበኞች አያት ቅድመ አያቶቻችን፣ ይሄንን የነጭ/የፈረንጅን ባሕሪ ጠንቅቀው ያውቁ ስለነበር* ***"ከፈረንጅ ብልኃቱን እንጂ ክፋቱን አይማሩም"*** *ያሉት። የእነሰዬና ድርጅታቸው ጭንቅላት ግን የዶሮ ጭንቅላት በመሆኑ የሚወስዱትና የሚማሩት ክፋትን እንጅ ብልኃትን አይደለምና፤ ይሄው ሂደታቸው ሁሉ "**ዶሮ ብታልም ጥሬዋን**" ሆኖ ነገረ ዓለማቸው በሙሉ፣ ከዚያችው ከጎጣቸውና ከመንደራቸው በላይ አላልፍ ብለው እንደዶሮዋ ጥሬያቸውን ብቻ በማሰብ አርጅተው ሊሞቱ አንድ ሐሙስ ቀራቸው። አይ ሞት! ሁሉን እኩል አድራጊ። ሞት፣ ነፍስህ አይማር። እነኝህ የዶሮ ጭንቅላት ያላቸው ወያኔና የወያኔ ሰዎች፣ ሁሉም እንደራሳቸው ይመስላቸዋልና "ኢሕአዴግ" የሚለውን ድሪቶ ሲደርቱ፣ ኢትዮጵያ የምትለዋን ቃል ብቻ ወስዱና ወያኔነታቸውን ሊደብቁ ባከኑ። ኢትዮጵያ የምትለዋን ቃል ስለለጠፉ ብቻ ግን፣ የወያኔን የገረጣ መንደርተኝነት ሊሸፍነው አልቻለም። ከትግራይ ዘለው ወደ መኃል አገር ሲነጉዱም በየረገጡበት ከተማና ገጠር ድብልቅልቅ ያለ ሠላማዊ ሠልፍ ገጠማቸው። ይህንን በየከተማውና ገጠሩ የገጠማቸውን የተቃውሞ ሠልፍ የተቋቋሙት፣ እነሰዬ የሚመሩት የ"ትግራይ ነጻ አውጭ" ነው ባሉት የወያኔ ጦር፣ ፊት ለፊት ያገኘውን በመግደልና፣ በሬሳ ላይ በመረማመድ ነው። ጉደኛው ወያኔ*

*በዚህ አላበቃም፣ አዲስ አበባ ሲደርስ የኢትዮጵያን ሕዝብ የጠየቀው እኒዲህ ብሎ ነበር- ወደ አዲስ አበባ እየገሠገስኩ ሳለ አለ ወያኔ! ለሕዝቡ (እነሱ "አማራ" ለሚሉት መሆኑ ነው ) ሕክምና ሳደርግ ነበርና የመጣሁት፣ ለዚያ ላወጣሁት የሕክምና ወጭ ኢትዮጵያ ትካሰኝ ብሎ በ"ኢሕአዴግ" ስም ከኢትዮጵያ ካሣ ጠየቀ። ኢትዮጵያ ይህንን እዳ ነው ተብሎ የቀረበባትን ክስ ለወያኔ 11.000.000(አስራ አንድ ሚሊየን) የኢትዮ.ብር ከኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ በገንዘብ ሰጠች። ለማን? "ለትግራይ ነጻ አውጭ ድርጅት" ህወሓት/ወያኔ ሃ! ሃ! ሃ1 ሃ!  ወዘተ..ወዘተ.. የዚህ ድርጅት ጉድ ተዘርዝሮ አያልቅም።*

*ወያኔ ጸረ ኢትዮጵያዊነቱን በኢትዮጵያ ምድር ለኢትዮጵያ ሕዝብ እሳካሁን እያሳየና በተግባር እየገለጠ ባለበት ሁኔታ፣ የዚህ ታሪክ ባለቤት የሆኑት እነ ሰዬና ገብሩ...ናቸው እንግዲህ ዛሬ ስለ ኢትዮጵያዊነትና ስለ "ኢሕአዴግ" ሊሰብኩንና ሊያጠምቁን የሚዳዱት?  ወይ "ኢሕአዴግ" ድንቄም!*

*<u>ኢሕዴን/ብአዴን (የኢትዮጵያ ሕዝብ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ)</u> ይህ ድርጅት በ"ኢሕአዴግ" ድሪቶ ተጠቅልሎ "የኢትዮጵያ ሕዝብ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ" ነኝ ብሎ ሲመጣ፣ ለተወሰነ ጊዜ በዚህ ስሙ አዲስ አበባ በወያኔ ጀርባ ታዝሎ ምኒልክ ቤተ መንግሥት እንደገባ ብዙ ሳይቆይ፣ በወያኔ ቀጭን ትዕዛዝ <u>ኢትዮጵያ</u> ያለውን ስሙን ቀይሮ ወደ ብሄረ አማራ ድርጅትነት ተቀየረና በአማራው ሕዝብ ላይ የጭቃ ጅራፉን ሰነዘረ። ልብ በሉ! ኢትዮጵያ የሚለውን ሐረግ ለጸረ-ኢትዮጵያው ወያኔ ትቶ፣ ወያኔ በሁለት ስም "በኢሕአዴግ" የኢትዮጵያ "መንግሥት" ነኝ እያለ፣ በወያኔው ደግሞ ይፋ ያልሆነውን በትግራይ "የትግሬ መንግሥት አቋም" የኢትዮጵያን ሃብት በሙሉ በወያኔው ድርጅት እንዲዘረፍ ተፈቀደለት። እነ ኤፈርት፣ ጉና፣ መሰፍን ኢንጅነሪንግ... ወዘተ የተባሉት የወያኔ ተቋሞች፣ ባለቤት የሌላቸውን እነሙገርንና ሌሎችን ፈጥፍጠው ጣሉ። እስከዛሬ ታዲያ ወያኔዎች የሚነግሩን "ሌሎች ክልሎች" እንደእኛ ክልል (ትግራይ ክ/ሃገር መሆኑ ነው) ማአከላዊው፣ "ፌደራላዊው" መንግሥት የሚሰጣቸውን ገንዘብ/በጀት በአግባቡ ስለማይጠቀሙበት፣ እንደኛ "እድገት" ሊያሳዩ አልቻሉም ይሉናል ሃ! ሃ! ሃ! ። ይህንን አባባል ደግሞ ሁሉም ወኔዎች (ወጣንም ገባንም የሚሉት ሁሉ) የዘወትር ንግግራቸው አድርገውታል።  እነኝህ ሰዎች እንደ ፍልሰፍናቸውና በውስጠ ደም ሥራቸው እንደሠረጸው ደዌአቸው ከዚያ "ክልል" (ከትግራይ መሆኑ ነው) ውጭ ተዋጊ፤ ጀግና፣ ረሃብን ታሪክ ያደረገና ሊያደርግ የሚችል ወዘተ...ዜጋ፣ በኢትዮጵያ ምድር ገና እስካሁን አልተፈጠረም ይሉና "ወርቆቹ" እኛ ግን ታታሪዎች ስለሆንን ቀድመን ሄድን ይሉናል ችግርና ችጋር ቀፍቃፊው ወያኔ/ኢሕአዴግ። ታዲያ ወያኔ ይሄን*

በሚልበት ጊዜ፣ የብሄረ አማራው ድርጅት ዋና ሰውና የአዲስ አበባው ምክትል ከንቲባ የነበሩት ቱባ ሰው፣ ለአንተ ነው የተደራጀሁት ያሉትን የአማራ ሕዝብ በወያኔ ከምትሰደብ፣ እኔው ያንተው የሆኑኩት ወኪልህ በራስህ ቋንቋ ቀለል አድርጌ ብነግርህ ይሻላል ብለው "የአማራው ሕዝብ ከየት ወደዬት" የሚል መጽሐፍ አበረክቱለት። አይይይ"ብአዴን/ኢሕአዴግዬ" ቂ ቂ ቂ ቂ። አቤት! አቤት አቤት! ዘመነ ግርንቢጥ ምን ጉድ ነው!። ሑፕሰሰሰሰ... ይቅርታ! እዚህ ላይ ይቅርታ! ሰዎችን አስቀጣ ይሆን? አይ! አይመስለኝም ምን አድርጌ። እኔ ታሪክ ማጣቀሴ ነው እንጂ ያለፈ፣ ያረጀ፣ ያፈጀ የ17 ዓመት ታሪክ ላወራ አይደለም። ደግሞስ! ካለፈው ታሪክ አይደለ እንዴ ደግ ደጉን ወስዶ የማይበጀውን በመተው ወደፊት ለመሄድ የሚቻለው። እንደዚያ መሰለኝ። የታሪክ ተመራማሪዎች እንደሚሉት ሁለት ወደፊት ለመሄድ አንድ ወደ ኋላ ታሪክን ቃኝት ማድረግ ይላሉ፣ ደግ ነው። ለክፉም ለደጉም ጥሩ ሃሳብ ነው እኔ 100% እስማማለሁ። በታሪክ ተመራማሪዎች አባባል።

ኦሕዴድ (የኦሮሞ ሕዝብ ዴሞክራሲያዊ ድርጅት)፥ ይህ ድርጅት በስሙ እንደሚታየው የኦሮሞን ሕዝብ እታደጋለሁ ባይ ነው። የኦሮሞን ሕዝብ እታደጋለሁ ብሎ በ"ኢሕአዴግ" ኮሮጆ የገባው ኦህዴድ፣ ከ "ኢሕአዴግ" ጋር ታዝሎ አዲስ አበባ ምኒልክ ቤተ-መንግሥት ሲገባ፣ የጠየቀው ጥያቄ ይሄንን "የአማራ" ምልክት የሆነ የምኒልክ ሃውልት ይፍረሰልኝ ብሎ ያዙኝ ልቀቁኝ በማለት ከአዲስ አበባ ሕዝብ ጋር "በሐውልቱ ይፈርስ አይፍረስ" ግብግብ ገጥመ። የአዲስ አበባ ሕዝብም አይፈርስም፤ የእኔነቴ ምልክት ከሚፈርስ እናንተን እሞግታለሁ ብሎ ባደረገው ተጋድሎ፣ ይህንን የወያኔ ጅራፍ ኦሕዴድን አሸንፎ ሐውልቱ እንዳይፍርስ ሆነ። ልብ በሉ! አዲስ አበባ ማለት ከመላው የኢትዮጵያ ክ/ሀገር የመጣ ኢትዮጵያዊ ሁሉ መናኸሪያውና የሚኖርበት መዲናው ነች። የ"ኢሕአዴጉ ኦሕዴድ" እንግዲህ የታገለው ከዚህ ህዝብ ጋር ነው ማለት ነው። ጉባይ! ዓይን አይከለክል ሰንቱን አየን!

"የደቡብ ኢትዮጵያ ህዝቦች ዴሞክራሲያዊ ህብረት" ወዘተ..... የመኮነኖች ዴሞክራሲያዊ ድርጅት ወዘተ... ሰንቱ ይቆጠራል። በ1983 ዓ.ም የነሰዬ/ገብሩው ወያኔ ከ70 የማያንሱ የጎጥ ድርጅት ፈልፍሎ፣ የተፈለፈለው የጎጥ ድርጅት ሁሉ ኢትዮጵያን ሠንጎ ያዘ። ምን ብሎ? ባሕረ ነጋሽ/ኤርትራ የኢትዮጵያ ሆና አታውቅም፣ ከነበረችም የአማራው ኢምፓየር ቅኝ ግዛቱ አድርጓት 30 ዓመት መከራዋን ሲያሳያት ኖረ። ዛሬ ግን "ነጽነቷን"

*ማግኘት አለባት ብለው ባህረ ነጋሽን ትሂድ ትሂድ ብለው ዳቦ/ሃምባሻ ከሻምፓኝ ጋር ቆርሠው አበባ እየበተኑ ፈረሙና "አሥመሪና ሽኮሪና’’’ ተብላ ተሸኘች። ሥረ መሠረቱ በእናቱም በአባቱም የትግራይ ሰው የሆነውና የትግራዩ ባላባት ኢሳያስ አፈወርቅ(ቂ)ም፣ ባህረ ነጋሽን ሌላ "አገር" ነች ሰጡኝ ብሎ ተረከበ አሉን። አሥመሪናም ሄደችችችችችችችችችችችች።*

*ጉድ ነው "ጉደኛ ገንፎ አድሮ ይፋጃል" አሉ። ኢትዮጵያ በዚህ ባሳለፍነው 17 ዓመት ስንቱን ፈተና ተፈተነች። ታዲያ እነሰዬ አንድ የሆነውንና የተዋለደውን የኤርትራን ሕዝብ እንዳለ ዓለምን አስገድድው በመጠየቅ ለወንድማቸው ለአፈወርቅ(ቂ) በፈቃዳቸው ሰጥተው እያለ፣ አሁን ዛሬ ከመለስ ጋር የተጣላነው በባድሜና ኤርትራዊ ስለሆነና ለኤርትራም ጥቅም የቆመ በመሆኑ ነው ብለው በሳቅ ያፈንዱናል። የት አባቴ ልግባ! ምን ዓይነት ሳቅስ ልሳቅ እስቲ ምከሩኝ ። እና **<u>"ኢሕአዴግ" ተብዬው እውነት የኢትዮጵያ</u> ሕዝብ ተቋም ወይም ንብረት ነው ማለት ይቻላል?** እንግዲህ እናንተው ፍረዱኝ ዘመዶቼ። ጉድ! ጉድ ! ጉድ!። ድሮ ኢትዮጵያን ወርሮ የነበረው ጣሊያን ያኔ በቦንብ ጋዝ ለጨፈጨፋቸው ኢትዮጵያኖች ካሣ እንዲከፍል በኢትዮጵያኖች ተጠይቆ (ምንም እንኳ በቂ ባይሆንም) ለኢትዮጵያ ከፍሏል። እነሆ! ያኔ የዘረፈዉን ሐውልታችንንም መልሷል። እርግጥ ነው ጣሊያን ይሄንን የዘረፈውን ሐውልታችንን ዛሬ ሲመልስ፣ የነሰዬ/ገብሩው ወያኔ ሲነገረነ እንደነበረውና እንደነገረን የሐጎስ ብቻ ነው ብሎ ሳይሆን የመለሰው፣ የሁሉም ኢትዮጵያዊ የገመዳ፣ የሉሊት፣ የሰባጋዲስ፣ የጫልቱ፣ የአሊ ሚራ፣ የጠና፣ የአባ ጃአፋር፣ የሸዋ ረገድ፣ የሞሚና፣ የአሸብር፣ የለምለም የሱሌማን...ወዘተ ነው ብሎ ለባለቤቱ ለኢትዮጵያ ሕዝብ አስረከበ። መኖር መልካም ነው ሁሉን ያሳያል አለሃምዱ ሊላህ፣ ቀሪውን ደግሞ ኢንሻአላህ! ዕድሜ ይስጠን። ልሠናበታችሁ ነው። አሉላ አባ ነጋ! እንዲህ ብለው ነበር አሉ።*

> *’’እኔ የሮማ ጠቅላይ ገዥ ሆኜ ስሄድ ያን ጊዜ ጣሊያኖችም ሰሐጢ ድረስ ሊመጡ ይችላሉ። አንዴ ክንዴን አሳይቻቸዋለሁ፣ እንደገና ከመጡም እደግማቸዋለሁ። የኢትዮጵያ የተፈጥሮ ወሰን ቀይ ባህር ሆኖ ኖሯል፣ ይኖራልም።’’ 1880 ዓ.ም አያችሁ ዘመኑን?*

*ታዲያ ይህንን ያሉት የኢትዮጵያ አርበኛ ሁለቴ ሞቱ። አንዱ በእግዚአብሄር/በአላህ እጅ የተፈጥሮ፤ 2ኛው ደግሞ በእነኝህ የታሪክ ጃርቶች ተገደሉ፤ እንዴት? ለመታሰቢያ የቆመው የአሉላ አባ ነጋ ሐውልት በእነ ኢሳያስ አፍወርቅ(ቂ) ፈረሰ አሉኝ። እድሜ ለወያኔ/ኢሕአዴግ! ዛሬ በ21ኛው ክ/ዘመን*

ደግሞ መንደረተኛው ወያኔ ዓለምን በሙሉ በመንደሩና በጎጡ ብቻ ይሰለዋል። ይህ ቡድን ከኢትዮጵያ ለአንዴና ለሁሌ ተነቅ፣ ደሞክራሲዊና የሕዝብ መንግሥት ማቆም ጊዜ የማንሰጠው ግዳጃችን ሊሆን ይገባል።አበቃሁ

**የሕዝብ ድምጽ ይከበር! የታሠሩ የፓለቲካ እስረኞች በሙሉ ይፈቱ! ኢትዮጵያ ለዘላም ትኑር! ቸር ይግጠመን**

ሴብቴምበር 28/ 2008